# ይድረስ ለብርቱዋ (ቁጥር 2)

ከከበቡሽ አየናቸው
ጥር15 2009

እሰይ የምሥራች ምሥር ብይ ብርቱካን፣
ምግብ ስለጀመርሽ ጭንቀቴ ቀንሷል፤
ያዘነልሽ ሁሉ በደስታ ተውጧል።
ዋናው ችግርማ የሁላችን ጭንቀት፣
ያንች መታሠር ነው ያንች መንገላታት።
ብርቱዬ ልንግርሽ ሕዝቡ ዳር እስከዳር፣
ካንች ጋር መሆኑን ይገልጻል በተግባር።
ፍትሕ ለተነፈጉት እሥረኞች በሙሉ፣
ሕዝቦች ተሰልፈው በዓለሙ ሁሉ፣
የኢሕአዴግን ጉድ ሲያጋልጡ ዋሉ።
ሁሉም በያለበት ቁጣው ገነፈለ፤
የእነመለስ ሚዛን እንደሣር ቀለለ።
የተዳፈነ እሣት ፍሙ ያልበረደ፣
ረመጡ ወጣ፤ የጨሰው ነደደ።
የትግል ጓዶችሽ ወንዶቹም ሴቶቹ፣
በጣም በአንች ኮሩ፤ ጠላቶችን ተቹ።
የዓለም ምንግሥታት የየአህጉሩ፣
እንደኛው ተሣነፈው ላልተው የነበሩ፣
የመለስን አቋም መመርመር ጀመሩ።
በእነርሱም የወጣው አዋጅ ተጨምሮ፣
ማስጠንቀቂያ በዝቷል ከአምናው ዘንድሮ፤
የሚበጅ አይመስልም ለእነመለስ ኑሮ።
ብርቱዬ ልንገርሽ ይኸ ግን ያስቃል፣
"የጨነቀው ዱቄት ከነፋስ ይጠጋል።"
በአባቶች ምሳሌ እንደሚባለው ቃል፣
የመለስ ኤምባሲ ዋሽንግተን ያለው፣
ለኦባማ ሹመት ድግሥ ሊደግሥ ነው።
ኦባማና ሌሎች የወያኔ ድምር፣
ድግሥ ተጠርተዋል በያዝነው ጥር ወር፣
አብረው እንዲዘፍኑ ከወያኔዎች ጋር።
ኦባማ አስቀድሞ ምርጫው ሳይጀመር፣
የኢትዮጵያን ጉዳይ ያውቀዋል በዝርዝር።
አሁንም ያለውን ያገር ቤቱን ችግር፣
የአንችንም ጉዳይ የሌሎችን ጭምር።
የወያኔ መንጋ ቢወድም ቢጠላም፣
በማታለል ብቻ አይኖርም ዘላለም፣
ኦባማም በፍፁም በሆዱ አይገዛም፣
የመረጠውን ሕዝብ ቃል ኪዳን አይረሳም፣
ግን የነርሱ ድፍረት ያስገርማል በጣም።
ብርቱዬ ጠንክሪ የመሸው ይነጋል፤
በሁሉም ትብብር ወጋገኑ ታይቷል።
ተወዳጇ እናትሽ ስለአንች ሲያወሩ፣

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com

በጣም ይታወቃል እንደተጀገሩ።
"አረ ለመሆኑ ብርቱካን እንዴት ናት?
በታሠረችበት በክፍሏ ማን አላት?"
ለሚለው ጥያቄ የጋዜጠኛው ቃል፣
እማማ ትልቋ እንደዚህ ብለዋል።
"ባለችበት ክፍል ሰውስ ማንም የለ፤
ግን የማይለያት እግዜር አብሯት አለ።"
ሐዋርያው መምህር ጳውሎስ እንዳለው፣
"እግዜር አብሮት ያለን የሚችለው ማነው?"
ያንችም ጠንካራ እምነት ከእናት ያገኘሽው፣
ለድል ያበቃሻል ብቻ እርሱን አስታውሽው።
ሕዝቡ አንድ ከሆነም ምንም አይሳነው።
        ብርቱዬ እህታለም ለዛሬው ልለይሽ፣
        በሌላ ደብዳቤ እስከምጠይቅሽ።
እባክሽ ለቴዲ ንገሪው ይኸን ቃል፣
"አይነጋም ወይ?" ያልኸው ሊነጋ ተቃረቧል፣
እንደስንቅ አቅማዳ ውሸታቸው ቀልሏል።

(በእህትነትሽ፣ በሴትነትሽ፣ በእናትነትሽ፣ በታጋይነትሽ፣
ከሁሉም በላይ በቆራጥ ኢትዮጵያዊነትሽ የማከብርሽ፣
እህትሽ ከበቡሽ።)

Document Produced by deskPDF Unregistered :: http://www.docudesk.com